# አዋጁ ፀደቀም አልፀደቀም....

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀ በኋላ በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ የፀጥታ ችግር በታየባቸው አንዳንድ የሃገራችን አካባቢዎች ከሞላ ጎደል ሠላምና መረጋጋት እየሰፈነ የመጣ ቢሆንም አሁንም በተወሰኑ የሃገራችን አካባቢዎች ችግሩ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር እንዳልዋለ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስቱ ሴክሬተሪያት ጽ/ቤት በቅርቡ ካወጣው መግለጫ ሰምተናል።

በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች የህዝቡ ሠላም መጠበቅ አለበት የሚል ቁርጠኛ አቋም በያዙ ጠንካራ የኦህዴድ አባላት ላይ ከአመፅ ሃይሎች ተደጋጋሚ ዛቻና ማስፈራሪያ እየደረሳቸው ከመሆኑም በላይ በአንዳንዶቹ ላይ በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው አባላት ላይ የግድያ እርምጃ የተወሰደባቸውም እንዳሉ ይሰማል። ሁከተኞቹ በእነዚህ አካባቢዎች መንገድ በመዝጋትና የፀጥታ ሃይሉን በመተናኮል ከሚያደርጉት አፍራሽ እንቅስቃሴ በተጨማሪ የእጅ ቦምብ በመወርወር በሰላማዊ ዜጎች ላይ የግድያና የማቁሰል ጉዳት እየፈፀሙ እንደሆነም የሚሰሙ ወሬዎች አሉ።

በሃገራችን ሰላምና መረጋጋት ላይ የተደቀነውን አደጋ መልክ ለማስያዝ በመንግስት የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በፓርላማ እንዳይፀድቅ ተፅዕኖ ለመፍጠርም በህዝብ ተመራጭ አባላት ላይ በማህበራዊ ሚድያ አማካይነት በተከታታይ ከሚያስተላልፉት አሉታዊ መልእክት በተጨማሪ በስልክና በአካል ጭምር ለማስፈራራት ጥረት ማድረጋቸውን እንደቀጠሉበት መሆኑ ይሰማል።

ሃገራችን በኢኮኖሚው መስክ ያስመዘገበችውን እጅግ የሚያኮራ እድገት ማሽመድመድ ዋና አላማቸው ያደረጉ እነዚህ የውስጥና የውጪ ጠላቶች የኢኮኖሚ አውታሮችን ዒላማ ያደረገ ጉዳት ለማድረስ ትከረት ሰጥተው እየሰሩ እንደሆነም የሚታዩ ምልክቶች አሉ። ለምሳሌ በምዕራብ ኢትዮጵያ በፊንጫ አከባቢ በርካታ ሔክታር ላይ የነበረ ለቀረጣ የደረሰ የሸንኮራ አገዳ በእሳት እንዲቃጠል ማድረጋቸው ተሰምቷል። ከዚህ ሌላ የሃገራችንን የኢኮኖሚ መዋቅር ከመሰረቱ በመለወጥ ረገድ ከፍተኛ ተስፋ የተጣለባቸውና ገና ከጅምሩ ለበርካታ ዜጎታችን የስራ እድል የፈጠሩ የኢንዱስትሪ ዞኖችን የማምረት ሂደት በማስተጓጎል የውጪ ኢንቨስተሮችን ለማስፈራራት ጥረት እያደረጉ ሲሆን በአንዳንድ የእንዱስትሪ ዞኖች ሁከትና ብጥብጥ እንዲነሳና ፋብሪካዎችንም በእሳት ለማጋየት የተደረጉ እንቅስቃሴዎች እንደነበሩ የሚሰሙ ወሬዎች አሉ።

እነዚህ የጥፋት ሀይሎች የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ቢታወጅም ባይታወጅ የሃገሪቱን ሰላምና መረጋጋት በማናጋት ስርዓቱን ለማፍረስ ቆርጠው የተነሱ በመሆናቸው አዋጁ በፓርላማ ፀደቀም አልፀደቀም የኢትዮጵያ መንግስትና የፀጥታ ሀይሎቻችን የሃገሪቱንና የህዝቡን ሰላም ለመጠበቅ በህገመንግስቱ የተሰጣቸውን ተልእኮ ከመወጣት የሚያግዳቸው ምንም አይነት ምድራዊም ሆነ ሰማያዊ ህግ ይኖራል ብለው ራሳቸውን በራሳቸው ባያታልሉ ይሻላል ባይ ነኝ፡፡

**ከበደ ዋቅጅራ**
**ከዱከም**
**የካቲት 22 ቀን 2010**